ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

Tel 202291 4217 mailling address: P.O.Box 73337, Washington Dc 20011

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
ነሐሴ 30 ቀን 2009 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

ሁሉም የየራሱን የተግባር ድርሻ መወጣት እየተሳነው ሲመጣ ፤ እርስ በእርሱ ጣት መጠቋቆም ይጀምራል። አንተ ትብስ፤ እኔ ልብስ መባባሉ ይቀርና ፤ አንዱ በሌላው ላይ፤ ያለ የሌለ ጥፋቱን እየደፈደፈ ፤ ራሱን ነፃ ለማውጣት ይጥራል ። ሌላውን ማጥላላት፤ የራሱን መወደድ ያተርፍልኛል ብሎ ይመኛል ። ይኽ ባኅርይ ደግሞ፤ ለፉክክር በር ይከፈታል ። ፍክክር፤ ውድድርን እየጋበዘ ፤ ጤናማ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንማ ኖሮ፤ የሚደገፍና የሚበረታታ ይሆን ነበር ። የተፈለገውንም ውጤት ለማስመዝገብ ያስችል ነበር ። ይኽ ሁኔታ ከተከሰተም ፤ በዕርግጥ፤ ፉክክርና ንትርክ እየተወገደ ፤ ቦታውን ለአዎንታዊ ውድድር በር ይከፍት ነበር ። ወደ አዎንታዊ ውድድርና ፉክክር መሄድ ከተቻለ ደግሞ፤ ሠላማዊ ጎዳና እየተከፈተ ሁሉም ተሳታፊ የሚሆንበት ዕድል ይፈጠር ነበረ ። ባለመታደላችን ምክንያት፤ ይኽንን ማግኘት ፤ እስካሁን ሳይቻል ቀርቷል ። ሁሉ ነገር ፤ በነበር አልቋል ። እስከ ዛሬ ድረስ !

ታዲያ ዛሬ ሁሉም፤ በበኩሉ፤ " **ይታደሷል እንጅ ይታገሷልን ?** " እያለ የአግራሞት ጥያቄ እየጠየቀ ራሱን እያጽናና መቆየትን መርጧል ብንል፤ ስህተት ነው ሊባል የሚችል አይመስለንም ። ምናልባት ፤ እራስን እያጽናኑ መኖር አይከፋም ይሆናል ፤ እራስን እያታለሉና እየደለሉ መቆየት ግን ፤ ዉሎ አድሮ፤ አሉታዊ አስተጋቦን እንጅ፤ ፋይዳን አያስገኝም ። እንዲያውም፤ " **ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ** " የሚል የለበጣ ፈገግታን ያስከትላል ። የማንኛውም ኅረተሰብ፤ ከዝቅተኛው ዕርከን የመድረስ ምልክቱ ፤ ተስፋ ቢስ መሆኑ ነው ። የሀገራችንም ሕዝብ ዛሬ የደረሰለት ነፃ አውጭ ኃይል በማጣቱ፤ ተስፋውን ቢቆርጥ ይታዘንለት ይሆናል እንጅ አይፈረድበትም ። ለአምሣ ዓመታት ያህል፤ በተፈራራቂ ጨካኝ አምባገነኖች መገዛት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚሸከመው በላይ ሆኖበታል ። ነገር ግን፤ " **እስኪያልፍ፤ ያለፋል** " **ቢል፤** " **አየ፤ ትለፋለህ እንጅ፤ ምን ያልፍልኻል?** " ሊባል አይገባውም ። ይኽንን ምፀት ፤ መስማት የሚፈልግ ህዝብ አይደለም ።

የፉክክር ቤት የሚዘጋው ጠፍቶ ክፍት በማደሩ ምክንያት ፤ የሌባና የዘራፊ ሲሳይ ሆኖ ይቀራል ። ቤቱ ተደፍሮ ፤ ባላቤቶቹ ተዋርደው፤ ንብረታቸው ተመዝብሮ፤ ቤተሰቡ ተበታትኖ፤ ልጆቹ ሰብሳቢ አጥተው ባውላላ ሜዳ ወድቀው ይቀራሉ። ይኽ ሁኔታ የሀገሪቱና የዜጎቿ ዕጣ- ፋንታ ከሆነ የአንድ ትውልድ ዕድሜን አስቆጥሯል። የአንድ ሀገር መሠረቱ፤ ጠንካራ ቤተሰብ እንደመሆኑ ፤ ቤተሰብ ከተናጋ፤ ሀገርም እንደ ሀገር የመቀጠሉ ዕድሉ፤ በሂደት እንደሚያከትም ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልም። ይኽንን በሚገባ የተገነዘቡ የሀገሪቱ ጠላቶች፤ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦችን እያፈለሷቸው ይገኛሉ ። **በተለይም ደግሞ ፤ የአማራውን ኅብረተሰብ !**

የሚፈልሱትን ቤተሰቦች ለማዳን ግን የሚደረግ በቂ ሙከራ አይታይም ። ቤተ ሰብ አፍላሾቹን እንቃወማለን ብለው የተሰለፉት ኃይሎችም፤ ትኩረታቸው ወደ አፍላሾቹ ያተኮረ ሳይሆን ፤ እርስ በእርሳቸው በፉክክር ላይ ጊዜያቸውን ያጠፉሉ። በመወዳደራቸው የተነሳ ፤ የግልም ሆነ የጋርዮሽ ኃላፊነት መሸከም አልቻሉም። በዚህ ምክንያት ሀገርና ሕዝብ በማያባራ ጥቃት ስር ይማቅቃሉ። ሰብሳቢ ያጣ አዝመራ፤ የአዕዋፋት መናሃርያ ሆኖ እንደሚቀር ሁሉ፤ የኢትዮጵያ ህዝብም ዛሬ ከበታኞች አደጋ ለመዳን፤ አንድነትን ኃይሎችን ፍለጋ እየባዘነ ይገኛል ።

እታገላለሁ የሚለውን ሠልፈኛ ቁጥሩ ለማወቅ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ብዛቱን ለመገመት እንኳን አልተቻለም ። አብዛኛው የጠራ ዓላማና ብሩኅ ራዕይ ስሌለለው፤ አቅጣጭ የሚያሳይ ካርታ (Road Map ) ማግኘት አልቻለም ። የአሰላለፉን ስልትና ዐላማ ያላወቀ ሠልፈኛ ደግሞ ፤ የጨረባ ተስካር ከማውጣት የዘለለ ሙያን ሊያሳይ አይችልም። ስልትን ሳያውቁ መሰለፍ፤ ከመርመስመስ የተሻለ ፋይዳ ማስመዝገብ አይሆንለትም። ብዛቱ ባይከፋም፤ ጥራት ከሌለው ግን እየተርመሰመሱ ከመቆየት በቀር፤ አንድ ርምጃ እንኳ ወደፊት መራመድ አይቻልም። ከብዛት ይልቅ፤ ለጥራት ትኩረት የሰጡ ቡድኖች ዓላማቸውን ግብ እንደመቱ ብዙ ማስረጃ ማጥቀስ ይቻላል ። ምክንያቱም፤ " **ዝምብ ቢጠራቀም ፤ ወስከምቢያ አይከፍትም** " የሚለውን ብሂል በሚገባ በመረዳታቸው ነበር። አፍራሽ ቡድኖች ፤የተርመሰመሰ አሰላለፍ ያለው ተቃዋሚ ስላጋጠማቸው ነው ዛሬ፤ ወያኔዎቹ በተቃዋሚው በረት ሰተት ብለው በመግባት እንደልባቸው እንዲያተረማምሱ ዕድል ያገኙት ። ምክንያቱም ፤ ይኸ ተቃዋሚ ነኝ የሚለው፤ ክፍል፤ ጎራውን አመንምኖ ፤ ውስጡን ከፍቶ ስለጠበቀው ብቻ ነው ። የዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ፤ ተቃዋሚው ክፍል፤ የጋራ ዓላማውን ዘንግቶ፤ እርስ በርሱ በሚያደርገው የውድድር አባዜ ሰለባ በመሆኑ ነው ። ምን ጊዜም ቢሆን ፤ የተቃዋሚው ክፍል ንዝኅላልነት እንጅ ፤ ለወያኔ ዕድሜው የሰጠው ፤ የወያኔ ብርታትና ዕውቀት እንዳልሆነ ሁሉም ያውቀዋል ። ወያኔዎቹም ራሳቸው፤ የተቃዋሚው ክፍል፤ አለመተባብር እንጅ ፤ የእነርሱ ብርታትና ኃይል እንዳልሆነ በሚገባ ይረዱታል ።

የፉክክር አባዜ ሰለባ የሆነው የተቃዋሚው ጎራ፤ ወደደም ጠላ፤ የሚከተሉትን ጎዳዮች አጢኖ በአስቸኳይ የተሻለ ሁኔታን ማምጣት ይጠበቅበታል ። ሀገሪቱን ከተቃጣባት ዐደጋ ለማውጣት ፈጣን ርምጃ መውሰድ ፤ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ሊወሰዱ የሚገባቸው ርምጃዎች ብለን የምናስባቸውን ኃሳቦች በቅደም-ተከተል፤ ለማስፈር እንፈልጋለን ፡-----------

**1ኛ.** ተመሳሳይ ዓላማና ግብ ያላቸው ክፍሎች ፤ ያለምንም ዝባ-ዝንኪና ቅድመ-ሁኔታ፤ በጋራ መቆም ይጠበቅባቸዋል ። ይኸንን ማድረግ ከቻሉ፤ ሌላው ቢቀር ከፉክክር ሰለባ ራሳቸውን አድነው፤ ቤታቸውን በመዝጋት፤ ከጠላት ሰርጎ ገቦች ትግላቸውን የመከላከል ክኽሎት ይኖራቸዋል። ይኸንን ማድረግ ከቻሉ፤ ፉክክርን ወደ አዎንታዊ ውድደር መለወጥ ይቻላቸዋል ። በጋራ ከቆሙ ደግሞ፤ የበረታ ዐቅም አግኝተው፤ ወያኔን ማቸነፍ አያቅታቸውም ። ቁርጠንኝትና ወሳኝነት የውጤት አብነቶች በመሆናቸው ፤ ቆርጦ በመነሳት፤ ወሳኝ ርምጃ መውሰድ አማርጭ አኖረውም ።

**2ኛ.** ሀገሪቱ የሁሉም ዜጎች ሀብትና ንብረት በመሆኗ ፤ተመሳሳይ ዓላማ ከሌላቸው ክፍሎችም ጋር ቢሆን ፤ ሀገሪቱን እንደ ሀገር ማቆየት አስፈላጊና ወሳኝ ስለሚሆን፤ ለሀገር መቆየት ሲባል ብቻ እንኳ፤ ከነኝህ ካልተመሳሰሉ ወገኖች ጋር በተፃፃሪ ከመቆም ይልቅ፤ ተቻችሎ መቆየቱ ይመረጣል ።የጋራን ሀገር በጋራ፤ ማቆየት ለሁሉም ይጠቅማል ። ተያይዞ አብሮ ገደል

ከመግባት ፤ ተባብሮ አብሮ መኖሩ ይበልጣል ። ኢትዮጵያ " ፈርሳ" የሌላው ቤት በጤና ሊኖር እንደማይችል መታወቅ አለበት ! " **ለትግራይ ያልሆነች፤ ኢትዮጵያ ትበጣጠስ** " ከሚሉ ዘረኞች ጋር ግን መተባበር ከንቱ ምኞት ነው !

**3ኛ.** እኛ፤ ሀገራችንን ኢትዮጵያን በአማራጭ / በልዋጭ (Option ) አናያትም። ዐልፋ- አሚጋችን ፤ ነች። ጩገሬታዋን/ ራስ- ማሏን ማጣት አንፈልግም። ኢትዮጵያ ! ኢትዮጵያ ! ስንል፤ ለከንቱ ውዳሴና ለመፈክር ማቀንቀኛ እሳቤ ሳይሆን፤ ዘላለማዊቷ ኢትዮጵያ፤ የመኖሯ ጉዳይ፤ ሌላ ምርጫ የማይኖረው በመሆኑ ነው ። ኀልውናዋ፤ ትላንት የነበረ፤ ዛሬም ያለ ፤ ነገም -ዘውትርም የሚኖር ፤ እስከ ዐለም ዳርቻ ፤ እስከ ዘመን መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል በመሆኑ ነው ። በመሆኑም ፤ የጋራ ሀገርን ከዐደጋ ለመከላከል፤ መፎካከር አስፈላጊ አይደለም። ምክንያቱም፤ የፉክክር ቤት ሳይዘጋ አድሮ፤ የሌቦች/ የዘራፊዎች መጫወቻ ይሆናልና ! የሚፎካከሩ የከብት እረኞች፤ ከብቶቻቸውን ለአውሬ አድጋ ያጋልጧቸዋል ። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎችም እንደዚሁ፤ የእርስ በእርስ መፎካከራቸውን ካላቆሙ፤ ሀገራቸው ተበታትና እንድትቀር መፍረዳቸውን ሊያውቁት ይገባቸዋል ። " **የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል !** " የተባለው ምሣሌያዊ አነጋገር የተቀረፀው ፤ እንዲያው በከንቱ አይደለም !

**4ኛ.** ዛሬ፤ በተጠያቂነት ፤ ሀገሪቱን በኃላፊነት ለመረከብም ሆነ፤ ከጥፋትም ለማዳን በዋናነት እኔ አለሁ የሚል፤ ኃይል ባለመኖሩ፤ ሁሉም በጎሪጥ እየተያየ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው።ይኸ ደግሞ፤ ኢትዮጵያ ፤ ዛሬ፤ አይዞሽ ! እኔ አለሁልሽ ! የሚላት ሰው ማጣቷን ያስገነዝባል ። ኢትዮጵያን በምልዕነት እንደ ሀገር መታየቷ እየቀረ ፤ በክልል መልከዐ-ምድር እየተሸነሸነችና በብሄርና በቋንቋ ተዋጽዖ እየተተለተለችም እየተፍረከረከችም የምትገኝ ሀገር ሆናለች ። ይኸ ሀቅ፤ የበርካታውን ዜጋ ፍርሃትና ስጋት እያጠነከረው በመሄድ ላይ በመሆኑ፤ እየዋለ እየደረም፤ ታዳጊውን ትውልድ እየመረዘው ይሄዳል የሚል ስጋት እያንዣበበ ነው። ይኸንን ማንዣበብ በቀላሉ ዐይቶ ማለፍ የሚቻል አይደለም ።ስጋቱን በንጭጩ ለመቅጨት ፤ከፉክክር ተላቅቆ ፤ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር መቀጠል አለባት የሚለው ዜጋ ሁሉ አበክሮ ሊያስብበት ይገባል ።

**5ኛ.** የሀገራችን የቅርብ ጊዜ ፖለቲካ ታሪክ እንደሚያስተምረው፤ " በኢትዮጵያ ሀገራችን ላይ የሚያንዣብበው ዐደጋ፤ የትም ሊደርስ አይችልም፤ ጉዳቱ ይኸንን ያህል አስጊ አይደለም " ተብሎ በንዝኅላልነት የሚታለፍ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በማንኛው መንግሥት ቢሆን ዕምነቱን ሊያሳድር አልቻለም ። አይችልምም። ምክንያቱም ፤ በቅርቡ የተለዋወጡት የአገዛዝ ሥርዓቶች፤ የሀገሪቱን ጥንተ- መሠረት ፍልስልሱን ከማውጣት ባሻገር፤ ለዘለዐለማዊቷ ኢትዮጵያ የሚሆን አንዳችም ተግባር ባለመስራታቸው ነው። በተለይ በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ መሆኑ ባይካድም፤ አሁን ሀገሪቷን የሚገዛት ዘረኛ ቡድን ፤ በባኅርይም ሆነ በድርጊት ኢትዮጵያዊ አለመሆኑን በተጨባጭ ያስመሰከረ መሆኑ ነው ። ይኸንን ሀቅ የተገነዘበ ሁሉ፤ ኢትዮጵያን የማዳን ኃላፊነት እንዳለበት ሊያውቀው ይገባል ፡፡ መካሪና ቀስቃሽ፤ አዛዥና ታዛዥ፤ ሰባኪና አስገዳጅ፤ ሳይኖር፤ እያንዳንዱ ዜጋ ሀገሩን የማዳን ተልዕኮ ፤የየራሱ- የየግሉ ኃላፊነትና ግዳጅ እንደሆነ ማንም ሊያሳውቀው አይገባም ። አይችልምም።

**6ኛ.** ኢትዮጵያ እንደ አንድ ሀገር መቀጠል አለባት ብሎ የሚያምን ዜጋ ሁሉ ፤ ሊገነዘበው የሚገባ ሌላ መሠረታዊ ጉዳይ አለ።ይኸውም፤ ሀገሪቱ መዳኗን ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያን አውቆ ፤ አንጠርጥሮና አብጠልጥሎ እንዲያውቅ ይጠበቅበታል ።

ኢትዮጵያን ማወቅ፤ ለለብ ለብ ፖለቲካ ፍጆታና መፈክር ወይም፤ ለዕለታዊ አቋም መግለጫና ድርጅታዊ ማሳወቂያ/ መገልገያ ሳይሆን፤ ጥልቀቱንና ምጥቀቱን ፤ ስፋቱንና ርዝመቱን፤ ሁሉ ያካተተ ሁለንተናዊ ዕውቀት ማለታችን ነው። እንደማነኛዎቹም የዐለም ሀገሮች ሁሉ፤ ኢትዮጵያ ሀገርችንም የራሷ የሆነ የተለየ ማንነትና ስብዕና አላት። ሀገራችን ልዩ ሀገር ( Unique ) ነች ሲባልም፤ ኢትዮጵያን፤ ኢትዮጵያ የሚያደርጋት ፤ ማንም የማይጋራት የራሷ አንጡራ ማንነትና ሰብዕና ( Identity ) አላት ለማለት ነው!

**ሀ.** ነዋሪዎቿ፤ ልዩ ልዩ ፤ብሄር ፤ ቋንቋ፤ የዘር ሀረግ፤ ታሪክ፤ ባኅልና ዕምነት ያላቸው ቢሆኑም፤ ይኽ ክስተት የሀገሪቱን ኁራማይሌነት (Mosaic ) ብልፅግና ፤ኃይልና ጥንካሬ ከማፀባረቅ አልፎ ተርፎ ፤ የዘረኞችና የበታኞች መሣሪያ ሊሆን እንደማይገባ መረዳት ያስፈልጋል ።

**ለ.** ምዕመኗ፤ ሦስት ታላላቅ ነባር ኃይማኖቶችን ያመልካሉ። እነርሱም፤ እንዳመጣጣቸው፤ ኦሪት፤ ተዋህዶ ቤት ክርስቲያንና እስልምና ናቸው ። ዜግቿ፤ ሦስቱንም የተቀበሏቸው በውዴታቸውና በፈቃዳቸው በመሆኑ፤ ሁሉም ምዕመናን ተስማምተው፤ ተቻችለው አብረው ኖረዋል ። የፖለቲካ መሪዎች ኃይማኖትን የአገዛዛቸው መሣሪያ / መጠቀሚያ ማድረጋቸው ሳይዘነጋ ማለት ነው ! ምዕመኑ ግን አብረው ተስማምተው ለዘመናት በጋራ መኖራቸው፤ ታላቅ ሕዝብ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው። ከነኝህ ሦስት ኃይማኖቶች ሌላ፤ በተለያዩ ባኅላዊ ዕምነቶች የሚያመልኩም አሉ። የአምልኮት ዕምነት የሌላቸውም ይኖራሉ ። ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ናቸው ። አብረው ኖረዋል ። ወደፊትም ይኖራሉ። **" ሀገር የጋራ ፤ ኃይማኖት ደግሞ የግል ነው "** የሚለው ዓይነተኛ መርኅ፤ የሀገራችን ማንነት ነፀብራቅ ሆኖ ቆይቷል ። ወደፊትም ይቀጥላል !

**ሐ.** በፊደል ተራ ሀ እና ለ የተገለጹትን መሠረታዊ ሃቆች ያላገናዘበ ዕውቀት ሰው ሰራሽ (Artificial ) ከመሆን አልፎ ተርፎ ፤ ፋይዳ ቢስ ነው። ፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን በነኝኽ ሀቆች ላይ የተመሠረተ የራሷ ብሄራዊ፤ መሠረታዊ፤ ቋሚ ሠነድ (Document ) እንዲኖራት ያስፈልጋል ። ይኽ ሠነድ ፤ **ቋሚ ሊሆን ይገባል ስንል፤ ዘለዓለማዊነቱ ፤ ከትውልድና ዘመን ተሻጋሪነቱ፤ ምክንያት ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከመንግሥታት መሪዎች ተጽዕኖ ነፃ ሆኖ፤ የሀገሪቱን ፤ታሪክ ፤ ባህል፤ የዜጎቿን አመለካከት ፤ ዕምነት ፤ ጠባይና መስተጋብር ፤ ነባር ማንነታቸውንም ሆነ፤ የወደፊት ምኞትና-ራዕያቸው (Aspiration ) አንፀባራቂ የሆነ ብሄራዊ/ኢትዮጵያዊ ሠነድ ማለታችን ነው።** እንደ ምሳሌ መሆን የሚችል የሌላ ሀገር ሠነድ መጥቀስ ካስፈለገ፤ አምስት መቶ ዐመታትን ዕድሜ ያስቆጠረው ማግና ካርታ (Magna Karta ) የተሰኘውን የእንግሊዞችን ብሄራዊ ሠነድ ነው። ይኽ ማግና ካርታ የተሰኘው ሠነድ፤ የእንግሊዞች የራሳቸው ማንነት መግለጫ ነው ። ታዲያ ኢትዮጵያ በጥንታዊነቷ የራሷን መለያ የሚመሰክር የራሷ ብሄራዊ ሠነድ ቢኖራት፤ የሚያኮራት ብቻ ሳይሆን ፤ ሀገራዊ ማንነቷንና ከሌላውም ልዩ የሚይደርጋትን የነፃነት ዕልውናዋን የሚረጋግጥላትም ሠነድ ይሆንላታል ። የሀገሪቱ ሊቃውንት -ጠቢባን ፤ የዕምነት መናንያን ፤ ምሁራንና ፈላስፋዎች ፤ አዛውንትና ኅልማሶች በዚኽ ጉዳይ ላይ ያስቡበት እንላለን። ይኽንን ማሳሰቢያ ለመጠቆም የምንፈልገው፤ ምን ጊዜም ቢሆን ፤ ለሀገርና ለህዝብ ይጠቅማል ብለን የምንመኘውን ራዕይና ተስፋ ለመግለፅ ካለን ቋሚ ዕምነትና ፍላጎት ነው። በትግላችን ታሪክም ይኽንኑ ስናሳስብ ቆይተናል ።

**መ.** እስካሁን ድረስ ሀገሪቱን የሚቆጣጥሯት ቡድኖች ሁሉ በምርጫ ሳይሆን፤ በጠበንጃ አፍሙዝ ኃይልና አመለካከት ላይ በተመሠረተ አገዛዝ ላይ በመሆኑ፤ ለየራሳቸው የሚያገለግላቸውን ደንብና አዋጅ እያወጡ ሕዝቡን ሲጨቁኑት ኖረዋል። ለይስሙላ የሚጽፏቸው ድንቦችና ሕጎች፤ ሕዝቡ ሳይመከረበት- ሳይወስንበት፤ በግድ የተጫነ ነብር ። ለአገዛዛቸው መሣሪያ ሊሆናቸው የሚችለውን መጨቆኛ ሠነድ፤ " ሕግ መንግሥት " ነው ብለው፤ ፍፁማዊ (Totalitarian) አገዛዝን ይመሰርታሉ ። ይህንን የተቃወመውን ዜጋ ሁሉ፤ የሀገሪቱን ህግ መንግሥት ጥሰሃል ብለው ያስሩታል፤ ያሰቃዩታል። ይገድሉታል ። ያሰድዱታል ።ምዕራባውያኑም፤ የእነርሱ የበላይ ጠባቂዎች ስለሆኑ፤ ከሕዝቡ አመፅ ይከላከሉላቸዋል ።

የዚህ ሁሉ ዐብይ ምክንያት፤ የዴሞክራሲ ሥርዓት አለመኖር መሆኑ አከራካሪ አይደለም። የዴሞክራሲ ሥርዓት፤ በህዝብ ትግልና ነፃ ምርጫ እንጅ፤ ካገዛዙ መልካም ፍቃድ እንዳማይገኝ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ ማንም ሊያውቅ አይችልም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ምክንያቱም፤ የደርጎቹና የወያኔዎቹ አገዛዝ ሥርዓት በሚገባ አስተምሮታልና ነው።

በዚህም ተባለ በዚያ ፤ የሀገራችን መከራና ፍዳ ለአንዴና ለሁሌም መወገድ ካለበት፤ የተቃዋሚው ኃይል፤ ከፉክክርና ከእርስ በእርስ ከመናቆር እራሱን ነፃ አድርጎና በኅብረት ኃይል ፈጥሮ ፤አስተማማኝ አማራጭ ይዞ መምጣት አለበት !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !